

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ

2019 የልማት እቅድ

ግንቦት /2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ተ.ቁ	የእቅዱ ይዘቶች	ገፅ
	ክፍል አንድ	**3**
1.1	ምህፃረ ቃል/Accronyms & Abreviations /	2
1.2.	አጠቃሎ /Executive summary/ 3	3
1.3	መግቢያ	4
1.4	የተቋሙ ራእይ፣ ተልእኮ እና እሴቶች	4-7
	ክፍል ሁለት	**8**
2.1.	መነሻ ሁኔታዎች	8-34
2.1.2.	ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ፡- የተቋሙ የሁኔታዎች ትንተና፣ /SWOT and PEST analysis	18
2.1.2.1.	ውስጣዊ ሁኔታዎች ትንተና (ጠንካራና ደካማ ጎኖች)	18
2.1.2.2.	ውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና (መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች)	20
2.2.	የተቋሙ ቁልፍ ችግሮች ትንተናና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎች	27
2.2.1.	የተቋሙ የቁልፍ ችግሮች ትንተና፣	26
2.2.1.	የተቋሙ ዋና ዋና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎችንና አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣	26
	ክፍል ሶስት	35
3.1.	የተቋሙ ዋና ዋና ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዓሊማዎችና ተግባራት እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶች እና ማስፈጸሚያ በጀት	35-47
3.1.1.	የቁልፍ ሥራዎች	29
3.1.2.	የዓበይት ሥራዎች ዕቅድ	32
3.1.2	ከግቦች የሚጠበቁ ውጤቶች	47
	ክፍል አራት	**50**
4.1.	የድርጊት መርሀ-ግብር እና ዕቅዱን ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች፤	50-
4.1.1.	የበጀት ዓመቱ የድርጊት መርሃ ግብር፤	51-70
4.1.2.	ዕቅዱን ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች፤	71-74

4.1.3	ማጠቃለያ	75

ምህፃረ ቃል/Accronyms & Abreviations /

- የተቀናጀ የበጀትና ወጪ መረጃ ሥርዓት / IBEX (Integrated Budget and Expenditure)
- የተቀናጀ የፋይናንስ ማናጅመንት መረጃ ሥርዓት/ IFMIS (Integrated Financial Management Information System)
- የኤሌክትሮኒክ መንግሥታዊ ግዥ ሥርዓት/e-GP (electronic Government Procurement)
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር /PFM (Public Financial Management)
- የመንግሥትና የግል አጋርነት /PPP (Public-Private Partnership)
- የውስጣዊ ጥንካሬና ድክመት እንዲሁም የውጫዊ መልካም አጋጣሚዎችና ሥጋቶች ትንተና መገምገሚያ ዘዴ /SWOT (Strengths, Weaknesses, Opportunities, Threats)
- ውጫዊ ሁኔታዎችን (ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ ከባቢያዊና ሕጋዊ) መገምገሚያና መተንተኛ ዘዴ/ PESTEL (Political, Economic, Social, Technological, Environmental, Legal.
- የዘላቂ የልማት ግቦች /SDGs (Sustainable Development Goals)
- ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች /KPIs (Key Performance Indicators)
- ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት /IMF (International Monetary Fund)
- የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም/UNDP (United Nations Development Programme)

ክፍል አንድ

1.1. አጠቃሎ /Executive summary/

የፋይናንስ ቢሮ የ2019 በጀት ዓመት የልማት ዕቅድ የተዘጋጀው በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 84/2016 የተሰጡትን ተልዕኮዎችና መዋቅራዊ ለውጦች መነሻ በማድረግ ነው። ተቋሙ በአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በ2022 የከተማዋን ሀብት በብቃት በማስተዳደር ፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ ልማት በማረጋገጥ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ከተሞች ውስጥ አንዱ ሆና ማየት የሚለውን ራዕይ በመያዝ እና ለከተማው ነዋሪ ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን የበኩሉን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል።

የ2019 በጀት ዓመትን የልማት ዕቅድ ሲዘጋጅ ሀገራዊ፣ ከተማዊና ተቋማዊ ሁኔታዎች ፣ የከተማ አስተዳደራችን ዕቅድ አፈጻጸም ሁኔታዎች ፣ የተቋሙ የትኩረት መስኮች፣ የ2018 በጀት ዓመት የተቋሙ የዋና ዋና ግቦችና ዓላማዎች አፈፃፀም ግምገማ፣ ከቁልፍ ሥራዎች ፣ የተቋም ግንባታና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ማሳደግ፤ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍታት፣ የአቤቱታ መወሰንና ማስፈጸም አቅም ማጎልበት እና ተቋማዊ የቅንጅት፣ የትብብርና የድጋፍ አሰራር ስርዓትን ማሻሻል፤ የዕቅድ/ሪፖርት ዝግጅት፣የኢንሸቲቭ ስራዎች አሰራር ሥርዓት ተግባራትን ለማሳካት የተዘጋጀ እቅድ ነው።

በተጨማሪ የሴክተሩ ባለድርሻ አካላት ትንተና እና የሴክተሩ የ10 ዓመት ፍኖተ ብልጽግና ዕቅድ የመጀመሪያ አምስት ዓመት /2014-2018/ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም እንደ መነሻ በመውሰድ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚሰጠውን አገልግሎት ፍትሃዊነትና ውጤታማነቱን ማሳደግ ግብ አድርጎ የተዘጋጀ እቅድ ነው።በዋነኛነት የከተማዋን የሕዝብ ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ማዘመን፣ የሀብት አሰባሰብና ምደባ ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፣ እና ዲጂታል የበጀትና የክፍያ ሥርዓቶችን (IFMIS, e-GP, IBEX፣ e-payment) ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ላይ ያተኩራል።

1.2. መግቢያ

የልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ የቢሮውን የፋይናንስ መዋቅርና አሠራር ከአዋጅ ቁጥር 84/2016 ድንጋጌዎች ጋር በማጣጣም፣ የከተማዋን የልማት ፕሮጀክቶችና መደበኛ ሥራዎች በበቂ የፋይናንስ ሀብትና ቀልጣፋ የክፍያ ሥርዓት መደገፍ ነው። በተጨማሪም የፋይናንስ ቁጥጥርና አዲት ሥርዓትን በማጠንከር ብክነትን መቀነስ፣ የከተማዋን የገቢና ወጪ ሚዛን በሳይንሳዊ መንገድ መምራት እና ለአገልግሎት ፈላጊዎች ግልጽና ተደራሽ አሠራር መዘርጋት ነው።

ቢሮው በመጀመሪያው 5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ታቅዶው ያልተከናወኑ እንዲሁም በ2018 በጀት ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራትን በልዩ ትኩረት እና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚሰጠውን አገልግሎት ፍትሃዊነትና ውጤታማነቱን ማሳደግ የሚያስችል እና በሁለተኛው አምስት ዓመት ስትራቴጂ ዘመን በዕቅድ የተያዙትን በላቀ ደረጃ ለመፈጸም የሚያስችል የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት ነው። የተቋሙ ዕቅድ ዝግጅት የሴክተሩ የ10 ዓመት ፍኖተ ብልጽግና ዕቅድ፣ የ4 ዓመት ከ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም፣እንዲሁም በተቋሙ የተቀረፀ የትኩረት መስኮችን በግባዕትነት ተጠቅመናል።

የልማት ዕቅዱ አራት ዋና ዋና ክፍሎች እና ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍል አንድ አጠቃሎ /Executive summary/፣ መግቢያ፣የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ መርሆዎች እና እሴቶች፣ በክፍል ሁለት መነሻ ሁኔታዎች እና ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ፣ የተቋሙ ቁልፍ ችግሮች ትንተና እና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎች፣ በክፍል ሶስት የተቋሙ ዋና ዋና ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዓላማዎችና ተግባራት እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶች እና ማስፈጸሚያ በጀት፣ በክፍል አራት የድርጊት መርሀ-ግብር እና ዕቅዱን ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች በማካተት ተዘጋጅቶ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1.2. የተቋሙ ራእይ፣ ተልእኮና እሴቶች

«በ2023 ዓ.ም በታማኝነት፣ በቴክኖሎጂና በልህቀት የዳበረ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት በመገንባት የከተማዋን ብልጽግና ዕውን ማድረግ፣

ተልዕኮ

«ዘመናዊና የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን እስከ ታችኛው መዋቅር በመዘርጋት፣ ፍትሐዊ ፖሊሲዎችን መቅረጽ፣ የሀብት ምንጮችን ማሳደግ እና የበጀት ተጠያቂነትን በማረጋገጥ የከተማዋን ሁለንተናዊ ልማት በማፋጠን የህዝብ ተጠቃሚነት ማሳደግ።»

እሴቶች (Core Values)

- **ታማኝነትና ቅንነት** (Integrity & Honesty)
- **ግልጽነትና ተጠያቂነት** (Transparency & Accountability)
- **ሙያዊ ልህቀት፣** (Professionalism & Excellence)
- **የትብብር መንፈስ** (Collaboration & Teamwork)
- **ለለውጥና ለፈጠራ ዝግጁነት** (Innovation & Adaptability)
- **ፍትሐዊነት**
- **የህዝብ አገልጋይነትን**

መርሆዎች (Operational Principles)

- **የሕግ የበላይነት** (Rule of Law)
- **ውጤታማነትና ቆጣቢነት** (Efficiency & Economy / Value for Money)
- **በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ** (Evidence-Based Decision Making)
- **ቀጣይነት ያለው ክትትልና ግምገማ** (Continuous Monitoring & Evaluation)
- **ዲጂታላይዜሽንና ተደራሽነት** (Digitalization & Accessibility)

የተግባርና ሀላፊነት ትንተና

የፋይናንስ ቢሮ የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 84/2016 **መሰረት የተቋቋሙ ሲሆን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፦**

1. **የመንግስት የግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ያስተባብራል፤ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤**

2. በከተማው አስተዳደር አካላት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የበጀት ጥያቄ እና የክፍለ ከተሞችን የበጀት ድልድል መርምሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በህግ መሰረት ያስተዳድራል፤
3. የፊስካል ፖሊሲ ያጠናል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ ውጤቱንም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
4. ባልተማከለ የበጀት አስተዳደር ሥርዓት መሠረት የክፍለ ከተሞችን የበጀት ድልድል ቀመር አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለክፍለ ከተሞች የሚሰጠውን የበጀት ድጎማ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
5. በገቢዎች ቢሮ የሚሰበሰበውን፣ በብድርና በእርዳታ የሚገኝ ገቢ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎችን ያስተዳድራል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
6. የግብር እና የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ የታሪፍ ማሻሻያ እንዲሁም አዳዲስ የገቢ ምንጭ ጥናት በማዘጋጀት እና/ወይም እንዲዘጋጅ በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
7. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች በከተማ አስተዳደሩ ስም ይበደራል፤
8. የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፍ ከዕርዳታ ሰጪ አገሮች ወይም ከተሞች እና ድርጅቶች ያፈላልጋል፤ ያስተባብራል ውል ይፈርማል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
9. የከተማውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፤ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
10. ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብና ገቢ ደረሰኞች፣ ቅጻቅፆች፣ መዛግብቶች ያሳትማል፤ እንዲታተም ያደርጋል፤
11. ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት በአግባቡ መፈጸሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤
12. ከከተማው አጠቃላይ ሃብት ጋር የተጣጣመ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶችን ተቀብሎ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያበለጽጋል፤ ያፀድቃል፤ ውል ይፈራረማል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

14. የከተማው አስተዳደር ዓመታዊ ሒሳብ አጠቃልሎ ይይዛል፤ በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ያስመረምራል፤ በግኝቱ ላይ ተመስርቶ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤
15. የከተማው የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤
16. የውስጥ ኦዲት በሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ በክፍለ ከተሞችና በወረዳዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
17. የውስጥ ኦዲት መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርቶችን ተቀብሎ ይገመግማል፤ የተገኙ ድክመቶች እንዲታረሙ ያደርጋል፤
18. የከተማው አስተዳደር አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፍና የማይተላለፍ የገንዘብ ሰነድችን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፤ ይጠብቃል፣

- የከተማዋን የማክሮ-ፋይናንስና የበጀት ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የገቢና ወጪ ትንበያ መሥራት።
- የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደርን በዲጂታል ሥርዓት (e-GP) መምራትና መቆጣጠር።
- የካፒታል ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ፍሰትና አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ።
- የውስጥ ኦዲት ሥርዓትን ማጠናከርና የፋይናንስ ዲሲፕሊን ማስከበር።

ዕሴቶች

- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ፍትሃዊነት
- ጥራት ያለው አገልግሎት
- በእውቀት መመራት
- ለለውጥ ዝግጁነት
- አሳታፊነትና በቡድን መስራት
- ለሀብት ውጤታማነትና ለልማት ስራዎች ዘላቂነት መጣር፣
- ሌብነትንና አድሎአዊነት መጸየፍ

ክፍል ሁለት፡ የአገራዊ፣ ከተማዊና የሴክተር ሁኔታ ትንተና

2.1. አገራዊና የአጠቃላይ ሁኔታ ትንተና

2.1.1. በአጠቃላይ ሁኔታ ትንተና/ግምገማ ላይ የፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ የጂኦግራፊያዊና የመሰረተ ልማት ሁኔታ ማካተት የሚያስፈልግ ሲሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ታሳቢ ተደርጓል፤

አገራዊ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ሁኔታ (Political & Legal Context)፦

ባለፉት 5 ዓመታት (2014-2018 ዓ.ም) በአገር አቀፍ ደረጃ የተካሄዱት ተቋማዊ ሪፎርሞችና የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 ለፋይናንስ ቢሮ አዲስ መዋቅራዊ ሽግግር ፈጥሯል። ይሁን እንጂ በአገር ደረጃ የመንግሥት የፋይናንስ ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውስጥ በከንቲባ ጽሕፈት ቤት፣ በፕላን ኮሚሽን እና በፋይናንስ ቢሮ መካከል በተለይም በካፒታል ፕሮጀክቶች ክትትልና በንብረት አስተዳደር ረገድ የሥልጣንና የአሠራር መደራረቦች በመኖራቸው የውሳኔ አሰጣጥ ፍጥነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው።

ለቀጣይ 2019 በጀት አመት ሕጋዊና መዋቅራዊ ግጭቶችን በተቋሙ አወቃቀር መሠረት ሙሉ በሙሉ በመፍታት ተጠያቂነትና ግልጽነት የሰፈነበት፣ ከተቋማዊ መደራረብ የጸዳ እና ከአገራዊ የፋይናንስ ሕጎች ጋር የተናበበ ዘመናዊ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ዋነኛ ፖለቲካዊና ተቋማዊ ትኩረት ይሆናል።

አገራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ (Economic Context)

ባለፉት 5 ዓመታት (2014-2018 ዓ.ም)፦ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ዕድገትና የከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋት የውስጥ ገቢን ለማሳደግ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። ሆኖም ግን፣ በአገር ደረጃ የተከሰተው ተከታታይ የዋጋ ንረት (Inflation)፣ የውጭ ምንዛሬ ተመን

ማስተካከያ ጫናዎች እና የፊስካል እጥረቶች በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም፣ በሜጋ ፕሮጀክቶች ወጪ መናር እና በበጀት ትንበያ ትክክለኛነት ላይ ከፍተኛ ማነቆ ፈጥረው ቆይተዋል።

በ2019 በጀት አመት አገራዊውን የማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተንተርሶ የማክሮ-ፊስካል ትንበያ አቅምን ማሳደግ፣ የዋጋ ንረቱን ታሳቢ ያደረገ ዘመናዊ የበጀት ዝግጅት መተግበር እና ከተለመደው የመንግሥት በጀት በተጨማሪ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን መፈለግ የኢኮኖሚ መረጋጋት ማረጋገጫ ስትራቴጂ ነው።

ማኅበራዊ ሁኔታ (Social Context)

ባለፉት 5 ዓመታት ከአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ወደ ዋና ከተማዋ የሚደረገው ፍልሰትና የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት ማደጉ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን (ትምህርት፣ ጤና፣ ትራንስፖርት፣ መኖሪያ ቤት) ለማቅረብ ሰፊ የበጀት ፍላጎት አስከትሏል። በሌላ በኩል፣ በታችኛው መዋቅር (በተለይም በወረዳዎች) የፋይናንስና አዲት ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተትና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ለተደጋጋሚ የአዲት ግኝቶችና ለሕዝብ ሀብት ብክነት መንስኤ ሆነው ቆይተዋል።

በ2019 በጀት አመት ደረጃቸውን የጠበቁ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፎችን (Competency Framework) በመዘርጋት የሰው ኃይልን ማብቃት፣ የበጀት ፍትሐዊነትን ማረጋገጥና የሕዝብ ተሳትፎ ያለበትን ግልጽ የበጀት አሠራር በማስፈን ማኅበራዊ ጥያቄዎችን በብቃት መመለስ ያስፈልጋል።

2.1.2. ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አንጻር (Alignment with Government Policies & Strategies)

የኢትዮጵያ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ (Homegrown Economic Reform) መሠረታዊ ግብ የሕዝብ ፋይናንስ ሥርዓትን ማዘመንና የመንግሥትን ወጪ በራስ አቅም መሸፈን ነው። የፋይናንስ ቢሮ ዕቅድ ይህንን ማክሮ-ኢኮኖሚያዊ ሪፎርም በከተማ ደረጃ ለማስፈጸም የተቃኘ ነው።

የቢሮው ስትራቴጂ ከአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (Homegrown Economic Reform 1.0 እና 2.0) መርሆዎች ጋር የተጣጣመ ነበር። የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር (PFM)

ማሻሻያዎችን በመተግበር ረገድ የፋይናንስ ሥርዓቱን ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማሳደግ ተሞክሯል። ሆኖም ግን፣ የአገሪቱን አዳዲስ የፖሊሲ ማሻሻያዎችንና መመሪያዎችን በፍጥነት ወደ ታችኛው አስፈጻሚ መዋቅር በማውረድና ወጥነት ባለው መልኩ በመተግበር ረገድ ክፍተቶች ነበሩ።

የመንግሥትን አዳዲስ የማክሮ-ኢኮኖሚ፣ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያዎችን መሠረት በማድረግ፣ የፋይናንስ ቢሮ መመሪያዎችንና አሠራሮችን ማዘመን ይኖርበታል። በተለይም የመንግሥት ወጪን የመቆጣጠር፣ የውስጥ ኦዲት ሥርዓትን የማጠናከርና የፋይናንስ ዲስፕሊንን የማስፈን አገራዊ ፖሊሲዎችን በቁርጠኝነት መተግበር ትኩረት ይሰጠዋል።

2.1.3. በአገር ደረጃ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር (Alignment with National Goals)

ዕቅዱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የ2030 የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) በተለይም ግብ 8 (የበለጸገ ኢኮኖሚ) እና ግብ 16 (ጠንካራ ተቋማትና ተጠያቂነት) እንዲሁም የአፍሪካ ሕብረትን "አጀንዳ 2063" ፍላጎቶች ያማከለ ነው። የበጀት ምደባው ድህነትን በሚቀንሱ ማኅበራዊ መሠረተ ልማቶች ላይ ያተኩራል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ መነሻ በማድረግ፣ አዲስ አበባ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና የብልጽግና መሪ ሞተር እንድትሆን የፋይናንስ ቢሮው የበጀት ድልድሉን ምርታማነትን በሚያሳድጉና የሥራ ዕድል በሚፈጥሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ አተኩሮ ሲሠራ ቆይቷል።

የከተማዋን የፊስካል አቅም ከአገራዊ የብልጽግና ግቦች ጋር በማስተሳሰር፣ የወጪ ውጤታማነትን ማረጋገጥና የፕሮጀክቶችን መጓተት ማስቀረት ዋነኛ ግብ ነው። እያንዳንዱ የተመደበ በጀት አገራዊ ምርታማነትንና የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጡን በቅርብ የሚከታተል ሥርዓት ይተገበራል።

2.1.4. ሀገራችን የተስማማችባቸው የዓለም አቀፍ ግዴታዎች አንጻር ("የዘላቂ የልማት ግቦች አጀንዳ 2030" እና "አጀንዳ 2063 የምንሻት አፍሪካ")

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተስማማችባቸውን የዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) መሠረት በማድረግ፣ የከተማዋ በጀት ድህነትን መዋጋት፣ ጥራት ያለው ትምህርት፣ ጸታን ያካተተ

ልማት እና ዘላቂ ከተሞችን መገንባት ላይ ያተኮሩ ሴክተሮችን በገንዘብ ሲደግፍ ቆይቷል። ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) እና ከUNDP መርሆዎች ጋር የሚስማሙ የሕዝብ ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ተጀምረዋል። ሆኖም ግን፣ እነዚህን አገራዊና ዓለም አቀፍ ግቦች በተደራጀ መልኩ ለመለካት የሚያስችሉ የቁልፍ አፈጻጸም አመልካቾች (KPIs) አጠቃቀም ደካማ ነበር።

በቀጣይ የልማት ዕቅዱን ከ"አጀንዳ 2030" እና "አጀንዳ 2063" ጋር ሙሉ በሙሉ ማስተሳሰር ያስፈልጋል። ለዚህም "መርሀ-ግብር ተኮር በጀት" (program Budgeting) ሥርዓትን በጥልቀት በመተግበር፣ ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ (Green Financing) እና ማኅበራዊ አካታችነትን የሚያረጋግጡ ፕሮጀክቶች በበጀት ድልድል ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል።

2.1.5. ከከተማ አስተዳደሩ የረጅም ጊዜ የትኩረት አቅጣጫዎችና መስኮች አንጻር (City Administration's Long-Term Focus Areas)

አዲስ አበባን ምቹ፣ ሳቢና ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ማዕከል ለማድረግ የሚከናወኑ የሜጋ ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ ፍሰት በዘላቂነት መደገፍና የካፒታል በጀት ቅልጥፍናን ማረጋገጥ የዚህ ዕቅድ ዋና መነሻ ነው።

የከተማ አስተዳደሩ አዲስ አበባን ምቹ፣ ውብና ዓለም አቀፍ የቱሪዝምና የኢኮኖሚ ማዕከል ለማድረግ ለያዘው የረጅም ጊዜ የትኩረት አቅጣጫ ቢሮው ሰፊ የፊስካል ድጋፍ አድርጓል። በተለይም ለኮሪደር ልማት፣ ለፓርኮች ግንባታና ለከተማ ውበት ሥራዎች የበጀት ቅድሚያ ተሰጥቷል። ሆኖም ይህ ትኩረት መደበኛ ማኅበራዊ አገልግሎቶችና የታችኛው መዋቅር የልማት ጥያቄዎች ላይ የበጀት ጫና እንዳይፈጥር የማመጣጠን ሥራ ፈታኝ ነበር።

የከተማዋን የረጅም ጊዜ ራዕይ ሳይነካ፣ የበጀት ድልድልን ሚዛናዊ በማድረግ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ጎን ለጎን ማስኬድ ያስፈልጋል። የከተማዋን ሜጋ ፕሮጀክቶች በፍትሐዊና ዘላቂ መንገድ ለመደገፍ የሚያስችል አገራዊ ፋይናንሻል ስትራቴጂ ይነደፋል።

2.1.6. ከከተማ አስተዳደሩ/ከሴክተሩ የረጅም ጊዜ የልማት ፕላን አኳያ (Sectoral Long-Term Development Plan)

በሴክተሩ የረጅም ጊዜ ዕቅድ መሠረት የፋይናንስ ሥርዓቱን ዘመናዊና ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የማድረግ ሥራ ተጀምሯል። የኢ-ግዥ (e-GP) ሥርዓት በተወሰኑ ተቋማት ላይ የተሳካ ቢሆንም፣ በሁሉም የከተማዋ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችና ወረዳዎች ላይ በተሟላ መልኩ አልተተገበረም። የመንግሥትና የግል አጋርነት (PPP) አማራጮችን በመጠቀም ረገድም የታቀደውን ያህል ውጤት አልተመዘገበም፤ ይህም ሰፊ የልማት ፍላጎትን በመደበኛ በጀት ብቻ ለመሸፈን አስገዳጅ አድርጎታል።

በቀጣዩ የ5 ዓመት (2019-2023 ዓ.ም)ም የልማት ፕላን የፋይናንስ ሴክተሩን የረጅም ጊዜ ግብ ለማሳካት አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የመንግሥትና የግል አጋርነት (PPP) ማዕቀፎችን በስፋትና በተደራጀ መልኩ መተግበር የግድ ይላል። በተጨማሪም የe-GP እና የIFMIS ሥርዓቶችን ሙሉ በሙሉ በማቀናጀት 100% የዲጂታል ፋይናንስና የግዥ ትግበራን ማረጋገጥና ብክነትን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ የሴክተሩ ቀጣይ ትልቅ ስኬት እንዲሆን ታቅዶ ይሠራል።

2.2. ከተማዊ ሁኔታ ትንተና (City-Level Context Analysis)

አዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት የኮሪደር ልማትን ጨምሮ ከፍተኛ መዋቅራዊና የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ትገኛለች። የከተማዋ የገቢ አሰባሰብ አቅም በዲጂታላይዜሽን ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣ ቢሆንም፣ የልማት ፍላጎቱና የበጀት ጥያቄው አሁንም ካለው የሀብት አቅርቦት በላይ ነው። በተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች (በተለይም በመሠረተ ልማትና ቤቶች ልማት) የፕሮጀክቶች መዘግየትና የዋጋ መናር በፋይናንስ ፍሰቱ ላይ ጫና ፈጥሯል። ቢሮው ይህንን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የበጀት አጠቃቀምን ከውጤት ጋር የማያያዝ (Performance-Based Budgeting) ሥርዓትን በማስፋፋት ላይ ይገኛል።

ይህ ከተማዊ ሁኔታ ትንተና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ ባለፉት አምስት ዓመታት (2014-2018 ዓ.ም) በተለያዩ የከተማዋ ክፍለ ኢኮኖሚዎች፣ የበጀት አጠቃቀም፣ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር እንዲሁም የፊስካል ሪፎርም ትግበራዎች ላይ ያስመዘገባቸውን ተጨባጭ ውጤቶች እና አሁን የተደረሰበትን የአፈጻጸም ደረጃ (KPIs) በዝርዝር ለመገምገም የቀረበ ነው።

2.3. ሴክተሩ/ተቋሙ ያለበት ሁኔታ (የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና)

የአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ የተመሠረተው የከተማዋን የፋይናንስ ሥርዓት በባለቤትነት ለመምራት ነው። ቢሮው መደበኛ የበጀት ዝግጅት፣ የሂሳብ መዝጊያ፣ የመንግሥት ግዥ ክትትልና ንብረት አስተዳደር ሥራዎችን ያከናውናል። በአሁኑ ወቅት አዲስ መዋቅርና የሥራ መደቦች የብቃት ማዕቀፍ (Competency Framework) የተዘረጋለት ቢሆንም፣ በየደረጃው ያለው አፈጻጸም ወጥ አይደለም።

የተቋሙ መሠረታዊ መረጃና ታሪካዊ ዳራ (Organizational Profile)

ሀ. አመሠራረትና ዓላማ (Establishment & Mandate)

ተቋሙ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሠረት) የተቋቋመ ሲሆን፣ ዋና ዓላማውም በከተማዋ ደረጃ ዘመናዊ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የሕዝብ ፋይናንስ አስተዳደር፣ የታክስ ፖሊሲ ጥናት እና የማክሮ-ኢኮኖሚ መዋቅር መዘርጋት ነው።

ተቋሙ የነበሩትን አሠራሮች ወቅታዊ በማድረግ፣ የከተማዋን የልማትና የካፒታል ፕሮጀክቶች በበጀትና በሀብት አጠቃቀም ረገድ ሥርዓት ለማስያዝ፣ የገቢ አቅምን በሳይንሳዊ ጥናት ለማሳደግ እና የፋይናንስ ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ነው።

ለ. የሚሰጡ አገልግሎቶችና መደበኛ ሥራዎች (Core Services & Mandate)

- በማክሮ-ፋይናንስና በታክስ ፖሊሲ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ።
- የተቀናጀ የሕዝብ ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቶችን (የበጀት ዝግጅት፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የውስጥ ኦዲትና የዕቃ ግዥ) በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (IBEX, IBEX/IFMIS , e-GP) መምራት።
- የአስተዳደሩን የአገልግሎት ታክሶኖሚ (Service Taxonomy) ማዘጋጀትና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን ስታንዳርዳይዝ ማድረግ።

ሐ. ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል (Structure & Human Capital)

ከተቋሙ ተልዕኮ አንጻር የጋራ ድጋፍ ሰጪ እና ዋና ዋና የሥራ ክፍሎችን (Core Processes) ያካተተ ሆኖ፣ የሥራ መደራረብን በሚያስቀርና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የተዋቀረ ነው።

ተቋሙ ከጁኒየር ኦፊሰር እስከ መሪ ባለሙያ (Junior to Lead Professional) የተዘረጋ የደረጃ ዕድገትና የክህሎት ማዕቀፍ (Competency Framework) ያለው ሲሆን፣ የሥራ ጫና እና የሰዓት ስርጭት ትንተናን (Workload Weight) መሠረት ያደረገ ምደባ ይከተላል።

መ. የከዚህ በፊት ውጤቶችና አሁን ያለበት ሁኔታ

በፋይናንስ ሥርዓት ሽግግር (ከበጀት አያያዝ ወደ የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት) እና የአገልግሎት ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ረገድ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ተቋሙ በአዋጅ ቁጥር 84/2016 የተሰጡትን አዳዲስ ኃላፊነቶች ተፈጻሚ ለማድረግና የአመራርና የባለሙያዎችን ብቃት (Performance Indicators) በመመዘን ላይ የሚገኝበት የሪፎርም ምዕራፍ ላይ ነው።

2.2.1. ከፊስካል ፖሊሲ እና ገቢ ጥናት አንጻር (Fiscal Policy & Revenue Study)

የከተማዋን ኢኮኖሚያዊ አቅም መሠረት ያደረጉ የማክሮ-ፊስካል ማዕቀፎች ተዘጋጅተዋል። ከታክስ ውጭ ያሉ የከተማ አስተዳደሩ የገቢ አማራጮችን (Non-Tax Revenues) ለማሳደግና የአገልግሎት ክፍያ ታሪፎችን ለማሻሻል የሚያስችሉ በርካታ የገቢ ጥናቶች ተካሂደዋል። በዚህም የከተማ አስተዳዳሩ ገቢ በአጠቃላይ ባለፉት አምስት ዓመታት የገቢ ዕቅድ በአማካይ በየዓመቱ 44.70 በመቶ ያደገ ሲሆን አፈጻጸሙ ደግሞ በ42.3 በመቶ ደርሷል70 **ቢሊየን የነበረው በ2018 በጀትዓመት ብር** 350.12 ቢሊዮን ብር የደረሰ መሆኑ፣ አሰባሰቡም ከፍተኛ ዕድገት ማሳየቱ በተለይ የአገር ውስጥ ገቢን (Domestic Revenue) የማሳደግ ስራዎች ተመሰርቷል። ከዚህ ውስጥ የታክስ መሠረቱን ማስፋት፡ የዲጂታላይዜሽን ስራዎች (e-Tax)፣የንብረት ታክስ እና የሊዝ ውዝፍ፣የንብረት እና የቤት ኪራይ ግብር ማሻሻያ፣የአገልግሎት ክፍያዎችን ማሻሻል ተጠቃሽ ናቸው። የመንግሥትና የግል አጋርነት (PPP) አማራጮችን ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችሉ መዋቅራዊና ሕጋዊ ማዕቀፎችም ተቀርጸዋል።

የከተማዋ የውስጥ ገቢ አቅም ማደጉ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም፣ አሁንም የገበያ መዋዠቅንና የዋጋ ንረትን (Inflation) አስቀድሞ በትክክለኛ መረጃ የሚተነብይ የላቀ የማክሮ-ፊስካል ሞዴሊንግ አቅም ክፍተት ይታያል።

የPPP አማራጮችን በተግባር በማዋል ረገድ የተጀመሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የሚያበረታቱ ቢሆንም፣ የከተማዋ ሰፊ የልማት ፍላጎት አሁንም በአብዛኛው በመንግሥት መደበኛ የፊስካል በጀት ላይ አተኩሯል።

2.2.2. ከበጀት ዝግጅትና አስተዳደር አንጻር (Budget Preparation & Administration)

የከተማዋን ፈጣን ዕድገትና የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶችን ታሳቢ ያደረጉ ዓመታዊና የመካከለኛ ዘመን የበጀት ድልድሎች ተዘጋጅተዋል። በወጪ መደብ ላይ የተመሰረተ የበጀት አሠራር ውጤት ተኮር በጀት" (program Budgeting) ሥርዓት በሙከራ ደረጃ ተጀምሯል።

የሴክተር መሥሪያ ቤቶችና የክፍለ ከተሞች የበጀት አጠቃቀም ፍላጎትና አፈጻጸም አለመመጣጠን አሁንም አልተቀረፈም።

በተለይም የፕሮጀክቶች የወጪ ግምት ጥናት (Feasibility Study) ትክክለኛ አለመሆን፣ በዓመቱ አጋማሽ ላይ ተደጋጋሚ ተጨማሪ በጀት (Supplementary Budget) እንዲጠየቅ በማድረግ የከተማዋን የፊስካል ዲስፕሊንና የሀብት ክፍፍል ሚዛን እየተፈታተነ ይገኛል።

2.2.3. ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አንጻር (Procurement & Asset Management)

የመንግሥት ግዥን ግልጽ፣ ፍትሐዊና ተጠያቂነት የሰፈነበት ለማድረግ የኤሌክትሮኒክ መንግሥታዊ ግዥ (e-GP) ሥርዓት ተቀርጾ በዋና ዋና የከተማዋ ማዕከላዊ መሥሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል። ይህም በማኑዋል የወረቀት ጨረታ አሰራር ስርዓትን በማስቀረት ረገድ ትልቅ እመርታ አሳይቷል።

የe-GP ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ወደ ታችኛው የክፍለ ከተማና የወረዳ መዋቅሮች ባለመውረዱ፣ አሁንም በርካታ ተቋማት በባህላዊ መንገድ ግዥ ይፈጽማሉ።

የመንግሥት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በአግባቡ ለመመዝገብና ለመቆጣጠር የሚያስችል የነጠረ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት (Database) ባለመኖሩ፣ የከተማዋን ንብረት በአግባቡ የማስተዳደርና በወቅቱ የማስወገድ (Asset Disposal) ሂደት ላይ ክፍተትና ብክነት ይስተዋላል።

2.2.4. ከመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቶች አንጻር (Integrated Financial Systems - IBEX & IFMIS)

የከተማ አስተዳዳሩ ወጪ አጠቃቀም እና ቁጠባ፣የኪራይ ወጪን የመቀነስ ስትራቴጂ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን የመንግስት የጋራ ቢሮዎች ግንባታ፣የተቋማት ውህደት፡ የወጪ አጠቃቀም ኖርም (Standardization of Spending)፣የነዳጅ እና የጥገና ቁጥጥር: የማዕቀፍ ግዥ ስርዓት (Bulk Procurement) ተግባዊ መሆኑ የመዋቅር ማሻሻያ (Structural Reforms) ተጠቃሽ ናቸው።

የከተማዋን የሒሳብ መዛግብትና የፋይናንስ ሪፖርት ጥራት ለማዘመን የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IBEX) እና የላቀው የሕዝብ ፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS) በሁሉም ማዕከላዊ አስፈጻሚ አካላትና ክፍለ ከተሞች ላይ ተዘርግቶ ጥቅም ላይ ውሏል።

በየደረጃው የሪፖርት አቀራረብ ፍጥነትና ጥራት ማሻሻያ ቢታይም፣ የ IBEX ሥርዓት እስከ ወረዳ መዋቅር ድረስ 100% አልደረሰም። ለዚህም የወረዳዎች የዲጂታል መሠረተ ልማት (ኔትወርክና የኮምፒውተር አቅርቦት) እጥረት ዋነኛ ምክንያት ነው።

በተጨማሪም በተደጋጋሚ የሚታዩ የኦዲት ግኝቶች፣ ሕጋዊ አሠራርን ያልተከተሉ ክፍያዎች እና ያልተወራረዱ ውዝፍ ሒሳቦች (Suspense Accounts) የፋይናንስ ሥርዓቱ የቁጥጥር (Internal Control) ክፍተት እንዳለበት ያሳያሉ።

2.2.5. ከመንግስት ፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ አንጻር (Project Monitoring & Evaluation)

በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚገነቡ የካፒታል ፕሮጀክቶች የሚመሩበትና የሚገመገሙበት አሠራር ተዘርግቷል። የፕሮጀክቶችን አካላዊና ፋይናንሻል ክንውን (Physical & Financial

Performance) ለማጣጣም የመስክ ምልከታዎችና ወቅታዊ የሪፖርት ግምገማዎች ተካሂደዋል።

በአፈጻጸም ደረጃ የፕሮጀክቶች መጓተት (Project Delay) እና ከተያዘላቸው በጀት በላይ ወጪ የመጠየቅ (Cost Overrun) ችግር የከተማዋ ትልቅ ማነቆ ሆኖ ቀጥሏል።

በአዋጅ ቁጥር 84/2016 መሠረት መዋቅራዊ ሽግግር ቢደረግም፣ በፋይናንስ ቢሮ እና በፕላንና ልማት ቢሮ መካከል በካፒታል ፕሮጀክቶች ክትትልና ባለቤትነት የነበሩ የአሠራር መደራረቦች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ መዘግየትን ፈጥረዋል።

2.2.6. ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ፕሮጀክቶች አንጻር (Civil Society Organizations Projects)

በከተማዋ ውስጥ በተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች (በትምህርት፣ ጤና፣ ሴቶችና ሕፃናት ልማት) ላይ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚያስገቧቸው የፕሮጀክት ሰነዶች ተገምግመው ስምምነቶች ተፈርመዋል። የእነዚህ ድርጅቶች ሀብት ከከተማዋ የልማት ቅድሚያ ትኩረቶች ጋር እንዲጣጣም የማስተናገድ ሥራ ተሠርቷል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ወደ ከተማዋ ይዘው የሚገቡትን የፋይናንስና የዓይነት ድጋፍ (Off-budget resources) ከተማ አስተዳደሩ ከሚመድበው መደበኛ በጀት ጋር በአንድ ማዕቀፍ አቀናጅቶ (Resource Mapping) የመምራትና የመቆጣጠር ሥርዓት ገና ያልዳበረ ነው።

ድርጅቶቹ ለፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከሚያወጡት አስተዳደራዊ ወጪ (Administrative Cost) ይልቅ ለሕዝብ ቀጥታ ተጠቃሚነት የሚውለውን በጀት (Operational Cost) 70/30 ሕጋዊ መደብ ጠብቀው እንዲንቀሳቀሱ በቅርብ የመከታተልና የመገምገም አቅም ላይ የባለሙያ ክፍተት ይታያል።

2.2.7. የተቋማዊ አቅም ግንባታ እና የኦዲት ቁጥጥር ዘርፍ

የሕዝብ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የውስጥ አዲት ቁጥጥር ሥርዓቶች ተዘርግተዋል። ከዋናው አዲተር የሚመጡ የውጭ አዲት ሪፖርቶችንም መሠረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ተሞክሯል።

ተደጋጋሚ የኦዲት ግኝቶች፣ ሕጋዊ አሠራርን ያልተከተሉ ክፍያዎች እና ያልተወራረዱ ውዝፍ ሒሳቦች (Suspense Accounts) አሁንም የተቋሙ ትልቅ ማነቆዎች ናቸው።

የሰው ኃይል አስተዳደሩን በተመለከተ፣ ለባለሙያዎች የሚሰጠው የሥልጠና ጥራትና ወጥነት የሌለው ከመሆኑም በላይ፣ ለቁልፍ የፋይናንስ ሥራዎች የሚመጥን ደረጃውን የጠበቀ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ (Competency Framework) ባለመኖሩ የባለሙያዎች ፍልሰትና የሥራ አፈጻጸም መዋዠቅ ይታያል።

2.3.1. የውስጣዊ ሁኔታ ትንተና (Internal Analysis)

የባለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈፃፀም እና የውስጥ/ውጭ ትንተና (SWOT Analysis)

የባለፉት ዓመታት/2014-2018/ አፈጻጸም ከታቀዱት ዋና ዋና ተግባራት (ገቢ ከመሰብሰብ፣ በጀት ከማስተዳደርና ሪፎርሞችን ከመተግበር) አንጻር ሲገመገም የሚከተሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችና ሥጋቶች ተለይተዋል፡-

- **ጠንካራ ጎኖች (Strengths):**
    - ለቁልፍ መደቦች ዝርዝር የብቃት መመዘኛ ማዕቀፍ (Competency Matrix) መኖሩ።
    - የሥራ ሂደቶችንና የአገልግሎት ዓይነቶችን በታክሶኖሚ ማኑዋል የመለየትና የመቅረጽ አቅም መኖሩ።
    - የዲጂታል አሠራሮችን (e-GP, IBEX/IFMIS, e-payment) ለመዘርጋት የተደረጉ መሠረታዊ ጅምሮች።
    - የአገልግሎት ታክሶኖሚ (Service Taxonomy) ማኑዋል እና የተሟላ የሥራ መደብ ዝርዝር መዘጋጀቱ/መኖር።
    - የIBEX/IFMIS እና የኢ-ግዥ (e-GP) ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት በዋና ዋና መሥሪያ ቤቶች መዘርጋቱ።
    - የበጀት አጠቃቀምና የሒሳብ አያያዝ መመሪያዎች መሻሻላቸው።

- **ደካማ ጎኖች** (Weaknesses):
    - **የባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት በተለይም የላቁ የማክሮ-ፊስካል ፖሊሲ ትንተናዎችንና የሕዝብ-የግል አጋርነት** (PPP) **ፕሮጀክቶችን በሚፈለገው ፍጥነት ለመምራት አለመቻል ማነቆ መሆኑ።**
    - **በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ ያሉ የፋይናንስ ባለሙያዎች የቴክኖሎጂና የክህሎት ክፍተት።**
    - **የውስጥ ኦዲት** (Internal Audit) **ሥርዓት ደካማ መሆንና የኦዲት ግኝቶች በፍጥነት አለመታረማቸው።**
    - **የፕሮጀክቶች የፋይናንስ ክትትልና ግምገማ** (Monitoring & Evaluation) **ሥርዓት ሙሉ በሙሉ አለመቀናጀት።**

2.3.2. የውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና (PESTEL) እና የመከላከያ ስትራቴጂዎች

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
1	ፖለቲካ (Political)	* የመንግስት የፋይናንስ ሪፎርምና ግልጽነትን የመደገፍ ቁርጠኝነት መኖር፣ * ለሕዝብ/መንግስት ፋይናንስ ሪፎርም የተሰጠ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር ቁርጠኝነት፣ * የፀረ-ሙስና ንቅናቄዎች መጎልበት። * የውጭ እርዳታና ብድር ፍሰትን የሚደግፉ የዲፕሎማሲ ስምምነቶች መኖር፣	* የፖለቲካ አለመረጋጋት በገቢ አሰባሰብ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣ * በታላቁ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ከጎረቤት አገሮች እና የቀይ ባህር ቀጣና ውጥረት፣ * በሰብዓዊ ዕርዳታ ስም የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት፣ * የፖሊሲ አፈጻጸም መዘግየት እና የተቋማት አደረጃጀት በተደጋጋሚ መቀያየር የሚፈጥረው የሥራ መስተጓጎል፣	* የፋይናንስ ሪፎርሙን ፍጥነት ለመጠበቅ አዳዲስ የአሠራር መመሪያዎችን ማውጣት፣ * ከአደጋ ስጋት ነፃ የሆኑ የገቢ አማራጮችን ማስፋፋት፣ * በፖለቲካዊ ለውጦች የማይናወጥ ጠንካራ ተቋማዊ አሠራር መገንባት፣ * የአሠራር ሥርዓቶችንና የአገልግሎት ምድብ/ታክሶኖሚን ተቋማዊ (Institutionalized) በማድረግ ከሰው ጣልቃገብነት ነፃ ማድረግ፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
2	ኢኮኖሚ (Economic)	* የአገር ውስጥ ምርታማነት ማደግ (የግብር መሠረትን ያሰፋል)፣ * የከተማዋ የኢኮኖሚና የንግድ እንቅስቃሴ ማደግና የገቢ አማራጮች መስፋፋት፣ * የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት መስፋፋት የገንዘብ ዝውውርን ማፋጠኑ፣ * አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፍሰቶች መኖር፣	* የዋጋ ንረት (Inflation) የበጀት የመግዛት አቅምን መጫኑ፣ የኑሮ ውድነት እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ዕጥረት መኖራቸው፣ * የሀገር ውስጥ የዋጋ ንረት የፕሮጀክቶችን ወጪ ማናሩና የግዥ ማዕቀፎችን ማዛባቱ፤ በመካከለኛው ምስራቅ አለመረጋጋት የነዳጅ ዋጋ መለዋወጥ፣ * ከተማው የሚያመነጨውን ያክል ገቢ መሰብሰብ አለመቻል፣ የኮንትሮባንድ፣ የጥቁር ገበያ እና የህገ ወጥና የጎዳና ላይ ንግድ መበራከት፣	* በጀት በሚታቀድበት ጊዜ የዋጋ ንረትን ያገናዘበ ክምችት (Contingency budget) መያዝ፣ * በማክሮ-ፊስካል ትንተና የታገዘ የበጀት ክለሳ ሥርዓት መዘርጋትና የዋጋ ማስተካከያ ቀመሮችን በውል መምራት፣ * የግብር አሰባሰብን ውጤታማ በማድረግ የበጀት ጉድለትን መሙላት፣ * የወጪ ቁጥጥር ሥርዓትን ማጥበቅና ቅድሚያ ለሚሰጣቸው

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
				ልማቶች ማዋል፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
			* የመንግስት ወጪ በብልሹ አሰራር፣ አመለካከትና ተግባር ምክንያት ለብክነት መዳረግ፣ * መንግስት ለተዘዋዋሪ ፈንድ የመደበውና ያበደረው ገንዘብ ከታለመለት ዓላማ ውጪ መሆን (ብድር በወቅቱ አለመመለስ)፣ * የልማት ድርጅቶች የመንግስት ትርፍ ድርሻ ፈሰስ አለማድረጋቸው፣ * የስራ አጥ ቁጥርን በሚፈለገው ደረጃ መቀነስ አለመቻል፣ * ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል አለመኖር (ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ)፣	* የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከልማት ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር መዘርጋት፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
3	ማህበራዊ (Social)	* የኅብረተሰቡ የግብር መክፈል ግንዛቤና ባህል እያደገ መምጣት፤ ለልማት፣ ለግልጽነትና ለፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ያለው ንቃተ-ሕሊና መጎልበት፣ * የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተጠናከረ መምጣት እና የማኅበረሰብ አቀፍ የልማት ተሳትፎዎች መጨመር፣ * የጤናና የትምህርት ሽፋን ተደራሽ መሆን፣ የማህበረሰብ ጤናን ለማሳደግ ማስስፖርት መስፋፋቱ፣ * የተማሪዎች ዩኒፎርምና ምገባ ድጋፍ ስርዓት በህብረተሰቡ ዘንድ እውቅና ማግኘቱ፣ * በከተማ አስተዳደሩ ሞጋች የሆነ የህብረተሰብ ክፍል መፈጠሩ። * የማህበራዊ ሴፍቲኔት እና የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠናክረው ተግባራዊ መደረጋቸው፣ * የህብረተሰቡን የኑሮ ጫናና የትራንስፖርት ችግር ለመፍታት አእእከተማው ካለው ገቢ ለልዩ ልዩ	* መንግስት አገልግሎት ፍላጎትንና ወጪን ማሳደጉ፤ ከፍተኛ የሆነ የሰው ፍልሰት (ከገጠር ወደ ከተማ) መኖር። * የትምህርትና የጤና አገልግሎት ጥራት ችግር መኖር፣ * ነዋሪውን በመንግስት ልዩ ልዩ ተግባራት ላይ በንቃት ማሳተፍ አለመቻል፣ * የጥገኝነትና የተረጂነት ስሜት መኖር፣ *በስነ-ምግባር የታነጸና በምክንያት የሚያምን ትውልድ አለመፈጠር፣ * በህብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰበሰብ ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ አለማዋልና ሂደቱን አለመፈተሽ፣ * የነዋሪው መሰረታዊ ፍላጎቶች (የመኖሪያ ቤት፣ ንጹህ ውሃና ምግብ) አለመሟላት፣ * ከፍተኛ የሆነ የሰው ሃይል ፍልሰትና እጥረት መኖር፤ * የገቢ አለመመጣጠን። * ድንገት የሚከሰቱ ተላላፊ	* የግብር አከፋፈልን ቀላልና ፍትሃዊ በማድረግ መንግስት አመኔታን ማሳደግ፣ * የዜጎችን ቻርተር (Citizens' Charter) ማሳተም፣ የአገልግሎት ጊዜን ማሳጠርና ቅሬታ ሰሚ ክፍልን ማጠናከር፣ * በጀት ሲመደብ ለተጋላጭ ማኅበረሰብ ክፍሎችና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ትኩረት መስጠት፣ * ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት። * ከተማ አስተዳደሩ በድንገት የሚከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች እና ተላላፊና ወረርሽኝ በሽታዎችን ለመከላከልና ስርጭቱን ለመግታት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
4	ቴክኖሎጂ (Technological)	* የኮር ፋይናንስ (IBEX/IFMIS) እና የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት (e-GP) መዘርጋት። * በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም ስርዓቱ መስፋፋቱ፣ የመረጃ አያያዝ በዳታቤዝ እየታገዘ መምጣቱ፣ * የአገር አቀፍ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ እና የኢንተርኔት መሠረተ ልማት መስፋፋት፣ * የሞባይል ባንኪንግ፣ የዲጂታል ግብር አሰባሰብ ቴክኖሎጂዎች ማደግ እና የባንክ አሰራር ስርዓት መዘመን፣ * የአይሲቲ መንደር መመስረቱ፣ * የሶሻል ሚዲያ አማራጮች መበራከት ለመረጃ ልውውጥ አመቺ ሁኔታ መፍጠሩ፣ * የሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) ለፋይናንስ ትንተና መጠቀም መቻል፣	* የመረጃ ደህንነት ስጋት/security/ እና የሳይበር ጥቃት (Cybersecurity) ስጋት መኖር፣ የዳታ መጥፋት ስጋት፣ * የኢንተርኔት፣ የኔትዎርክና ኤሌክትሪክ መቆራረጥ፣ * የሠራተኞች የቴክኖሎጂ ክህሎት ውስንነት፣ * የሶሻል ሚዲያን ለመልካም ነገር አለማዋል እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት፣	* የሳይበር ደኅንነት ሥርዓትን፣ የዳታ ማዕከል (Data Center) ደኅንነትን ማደስ፣ ጠንካራ የፋየርዎል ሥርዓትና የዳታ ምትኬ (Backup) አደረጃጀትን ማጠናከር፣ * ለሠራተኞች ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት፣ * ከተለዋጭ የኢንተርኔት አቅራቢዎች ጋር መሥራት፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
5	ከባቢያዊ (Environmental)	* ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ (Green Economy) እና የአየር ንብረት ለውጥን የሚደግፉ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ የውጭ ፈንዶችና ድጋፎች መኖር፣ * የአካባቢ ጥበቃ ፕሮጀክቶች አዲስ የገቢ ምንጭ መፍጠራቸው፣ * የወረቀት አልባ (Paperless) አሠራርን የመተግበር ዕድል መኖር፣	* የአየር ንብረት መዛባት (ድርቅ/ጎርፍ) በከተማዋ መሠረተ ልማት ላይ ድንገተኛ የበጀት ጫና መፍጠራቸው፣ * በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የግብር ከፋዮች የመክፈል አቅም መዳከም፣ * በሚሰሩ የልማት ስራዎች የህብረተሰቡ የኔነት ስሜት አናሳ መሆን እና ለኑሮ ምቹ የሆነ አካባቢ አለመኖር፣ * የሀብት መመናመን ፣	* ለአደጋ ጊዜ መቋቋሚያ የሚሆን የተጠባባቂ በጀት (Emergency Fund) በልዩ ሁኔታ መመደብ፣ * ከአረንጓዴ ፈንድ ድርጅቶች ጋር አጋርነት በመፍጠር ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጭ መሳብ፣ * የቢሮውን አሠራር ሙሉ በሙሉ በዲጂታል በማድረግ የወረቀት ወጪን መቀነስ፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
6	ሕጋዊ (Legal)	* አዋጅ ቁጥር 84/2016 ግልጽ የሥልጣንና ተግባር ወሰን ማስቀመጡ፣ * አዳዲስ የፋይናንስና የግብር ሕጎች፣ እንዲሁም የኮንትራትና የግዥ ሕጎች መሻሻላቸው፣ መዘመናቸውና ግልጽ መሆናቸው፣ * የከተማ አስተዳደሩ የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ መከለሱ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ መሻሻሉ፣ * መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ /BPR/ በከተማ ደረጃ መከለሱ፣ * የዓለም ባንክ እና የገንዘብ ሚኒስቴር የፋይናንሽያል ማኔጅመንት ስርአቱ ላይ የአቅም ግንባታ እገዛ የሚያደርጉ	* ከአዋጁ በኋላ የሚወጡ የፋይናንስና የግዥ ዝርዝር መመሪያዎች መዘግየት፣ * አዳዲስ ሕጎች ከነባር አሠራሮች ጋር በፍጥነት አለመጣጣም፣ የሕግ አፈጻጸም መዘግየትና የዳኝነት ሥርዓት መጓተት፣ * በኦዲት እና የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ አፈጻጸም ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ በሚፈለገው ልክ አለመውሰድ፣ * የባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎች የውስጥ ቁጥጥር ስርአትን በአግባቡ እንዲዘረጋ ቁርጠኛ አለመሆናቸው፣ * የግዢና ንብረት ቅሬታና አቤቱታ	* የሕግና መመሪያዎች ትርጓሜ ለፈጻሚዎች በሥልጠና በግልጽ እንዲደርስ ማድረግ፣ * ረቂቅ መመሪያዎችን ከሚመለከታቸው የሕግ አካላት ጋር በመሆን ቀድሞ አዘጋጅቶ ማጽደቅ፣ ግጭት የሚፈጥሩ መመሪያዎችን በወቅቱ መለየትና ማሻሻያ ማቅረብ፣ * ከኦዲትና ሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በመቀናጀት የፋይናንስ ተጠያቂነትን ማረጋገጥና የሕግ የበላይነት መከበር ተጠያቂነትን ማስፈኑ፣

ተ.ቁ	ውጫዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)	ስጋቶች (Threats)	ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች (Strategies)
		መሆኑ፣	ወቅታዊ ምላሽ አለመስጠት፣	

ዋና ዋና ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂያዊ ምክረ-ሀሳቦች (Key Strategic Takeaways)

1. **የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ማፋጠን፦** የቴክኖሎጂ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም የገቢ አሰባሰብንና የወጪ ቁጥጥርን ማዘመን የሳይበር ስጋቶችን አስቀድሞ መከላከልን ይጠይቃል።
2. **የበጀት የመቋቋም አቅም** (Financial Resilience) **መገንባት፦** የዋጋ ንረትንና የአየር ንብረት መዛባትን የመሳሰሉ ስጋቶችን ለመቋቋም የተጠባባቂ በጀት አያያዝን ሥርዓት ማጠናከር ወሳኝ ነው።
3. **የሕግ የበላይነትና ተጠያቂነት፦** የተሻሻሉ የፋይናንስ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የአዲት ግኝቶችን መቀነስና የሕዝብ ሀብት ብክነትን መግታት ይገባል።

ክፍል ሦስት፡ የሴክተሩ/የተቋሙ ያገባኛል ባዮች፣ ቁልፍ ችግሮችና የአፈጻጸም ስትራቴጂዎች ቀረጻ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮን መዋቅር፣ ተልዕኮና ስልጣን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀው የባለድርሻ አካላት (Stakeholders) እና የቁልፍ ችግሮች ትንተና፣ እንዲሁም ቀጣይ የአፈፃፀም ስትራቴጂዎችና አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

3.1. የፋይናንስ ቢሮ ያገባኛል ባዮች /አጋር አካላት/ ትንተና

3.1.1. የተቋሙ ያገባኛል ባዮች / የአጋሮች ትንተና (Partners & Claimants)

በቢሮው የእለት ተእለት ስራ፣ የፖሊሲ አቅጣጫ እና የሀብት አጠቃቀም ላይ ቀጥተኛ ፍላጎት፣ መብት ወይም የይገባኛል ጥያቄ ያላቸው አካላት ሲሆኑ የሚከተሉትን ተቋማት ያካትታል።

- **የከተማው ከንቲባ ፅህፈት ቤት እና የስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት፦**
    - ፍላጎት/ድርሻ፦ የከተማዋን በጀትና ፋይናንስ በልማት እቅዶች (ከ2016-2030 የረጅም ጊዜ እቅድ ጋር በተጣጣመ መልኩ) መምራት፣ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ውጤታማነትን ማረጋገጥ።
    - ተፅዕኖ፦ ከፍተኛ የፖሊሲና የውሳኔ ሰጪነት ሚና አላቸው።
- **የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት (ምክር ቤቱ)፦**
    - ፍላጎት/ድርሻ፦ የከተማዋ አመታዊ በጀት በህግ እንዲጸድቅ ማድረግ፣ የህዝብ/ፐብሊክ ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን መቆጣጠር እና የኦዲት ግኝቶችን መከታተል።
- **የከተማዋ ነዋሪዎች እና ግብር ከፋዮች፦**
    - ፍላጎት/ድርሻ፦ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ፍትሀዊ የከተማ አገልግሎት ማግኘት፣ የከፈሉት ግብር ለታለመለት የልማት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ (የበጀት ግልጽነት)።
- **የፌደራል ገንዘብ ሚኒስቴር፦**
    - ፍላጎት/ድርሻ፦ የማክሮ-ኢኮኖሚና ፊስካል ፖሊሲዎች መናበብ፣ የፌደራል ድጎማዎች አጠቃቀም መከታተል፣ እና ሀገር አቀፍ የፋይናንስ ስርዓት (Public Financial Management - PFM) መከበሩን ማረጋገጥ።

3.1.2. የባለድርሻ አካላት ትንተና (Stakeholders Analysis)

ባለድርሻ አካላት በቢሮው ውሳኔዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ወይም በቢሮው ውሳኔዎች ተፅዕኖ የሚያርፍባቸው ተቋማት ናቸው።

- **የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች (ሴክተር ቢሮዎች - ጤና፣ ትምህርት፣ መንገድ፣ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ወዘተ)፦**
    - ሚና፦ የበጀት ተጠቃሚና አስፈፃሚዎች ናቸው።
    - ግንኙነት፦ ወቅታዊ የበጀት ዝውውር፣ የካፒታል ፕሮጀክቶች ፋይናንስ አቅርቦት እና የፋይናንስ መመሪያዎች ተፈጻሚነት ላይ በጋራ ይሰራሉ።
- **የከተማው ፕላንና ልማት ቢሮ፦**
    - ሚና፦ ከከተማዋ የልማት እቅድ ጋር የተጣጣመ የካፒታል በጀት አመዳደብን ማቀናጀት።
    - ግንኙነት፦ በበጀት ዝግጅትና በፕሮጀክቶች ግምገማ ወቅት የጠበቀ ትብብር ያስፈልጋቸዋል።
- **የገቢዎች ቢሮ፦**
    - ሚና፦ የከተማዋን የውስጥ ገቢ ሰብሳቢ ተቋም።
    - ግንኙነት፦ የፊስካል ፖሊሲና የገቢ ጥናት ስራዎችን በጋራ በመስራት የከተማዋን የበጀት አቅም (Fiscal Space) ይወስናሉ።
- **የከተማው ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት፦**
    - ሚና፦ የፋይናንስ አጠቃቀምንና ህጋዊነትን መመርመር።
    - ግንኙነት፦ የኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የፋይናንስ ዲሲፕሊን ማስተካከል ላይ በጋራ ይሰራሉ።

3.1.3. የተባባሪ አካላት ትንተና (Collaborators/Allies)

የፋይናንስ ቢሮን ስልታዊ ግቦች ለማሳካት በቴክኒክ፣ በቴክኖሎጂ እና በገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ናቸው።

- **ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች (የዓለም ባንክ፣ IMF፣ UNDP ወዘተ)፦**

- የድጋፍ ዘርፍ፦ የህዝብ/ፐብሊክ ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያ (PFM Reform) ድጋፍ፣ የከተማ ልማት ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ፋይናንስ እና የአቅም ግንባታ።

- **የቴክኖሎጂ እና የመሰረተ-ልማት አቅራቢዎች (ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ባለስልጣን፣ ኢትዮ ቴሌኮም)፦**
  - የድጋፍ ዘርፍ፦ የዲጂታል ፋይናንስ ስርዓቶችን (IBEX/IFMIS , e-GP, IBEX) መተግበር እና የሳይበር ደህንነታቸውን ማረጋገጥ።
- **የግል ባለሀብቶች እና የፋይናንስ ተቋማት (ባንኮች)፦**
  - የድጋፍ ዘርፍ፦ በመንግስትና በግል አጋርነት (Public-Private Partnership - PPP) ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ፣ እና የከተማውን የክፍያና የገንዘብ ዝውውር /e-payment/ ስርዓት ማዘመን።

3.1.4. የሴክተሩ/የተቋሙ የቁልፍ ችግሮች ትንተና

የፋይናንስ ቢሮ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር (በተለይም በአዋጅ ቁጥር 84/2016 እና ተያያዥ መመሪያዎች) መሰረት ስራውን ሲያከናውን የሚገጥሙት ዋና ዋና ስልታዊና ተግባራዊ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፦

የመዋቅርና የሃላፊነት መደራረብ (Structural Overlaps)፦

- በፋይናንስ ቢሮ፣ በፕላንና ልማት ቢሮ እና በከንቲባ ፅህፈት ቤት መካከል በካፒታል ፕሮጀክቶች ምርጫ፣ ክትትልና የንብረት አስተዳደር ዙሪያ ግልጽ የድንበር መለየት ክፍተቶች መኖር።

የዲጂታላይዜሽን እና የተቀናጀ የፋይናንስ ስርዓት (IBEX/IFMIS /e-GP) ውስንነቶች፦

- የመንግስት ግዢና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል አለመቀየር፣ በየደረጃው ባሉ አስፈፃሚዎች ዘንድ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተት መኖር እና የስርዓት መቋረጦች (Downtime)።

የበጀት ስነ-ስርዓት (Fiscal Discipline) እና የኦዲት ግኝቶች መደጋገም፦

- በአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ዘንድ የበጀት አጠቃቀም ህጋዊነት ጉድለት፣ ህገ-ወጥ ክፍያዎች እና የተደጋገሙ የኦዲት ግኝቶችን በፍጥነት የመፍታት ውስንነት።

የፕሮጀክቶች አፈፃፀም መጓተትና የወጪ መናር፦

- የካፒታል ፕሮጀክቶች ጥናት ሳይጠናቀቅ በጀት መያዝ፣ የኮንትራት አስተዳደር ድክመት እና ይህንን ተከትሎ የሚመጣ የከተማዋ ህዝብ የልማት ጥያቄ አለመመለስ።

የሰው ሃይል አቅም እና የብቃት ማነስ (Competency Gaps)፦

- በማክሮ-ፊስካል ፖሊሲ ትንተና፣ በዕዳ ማስተዳደር እና በPPP ፕሮጀክቶች ስምምነት ዙሪያ ከፍተኛ ባለሙያዎችን (Lead Professionals) የመሳብና የማቆየት (Retention) ችግር።

3.2. የሴክተሩ/የተቋሙ ዋና ዋና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎችንና አቅጣጫዎችን መንደፍ

የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እና ከአጋር አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚከተሉት ስልታዊ አቅጣጫዎች ተነድፈዋል፦

1. የህዝብ/ፐብሊክ ፋይናንስ አስተዳደርን (PFM) ማዘመንና ዲጂታላይዝ ማድረግ

- **ስትራቴጂ፦** የIBEX/IFMIS (Integrated Financial Management Information System)፣ e-payment እና የe-GP (electronic Government Procurement) ስርዓትን እስከ ወረዳ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ማውረድና ከተማ አቀፍ ማድረግ።
- **አቅጣጫ፦** የወረቀት አልባ (Paperless) የፋይናንስና የግዢ ስርዓትን በመዘርጋት ግልጽነትን ማረጋገጥና ብክነትን መቀነስ።

2. **የበጀትና የፊስካል ፖሊሲ ትንተና አቅምን ማጠናከር**

- **ስትራቴጂ** ከገቢዎች ቢሮ ጋር በመቀናጀት የከተማዋን የውስጥ ገቢ አቅም የሚያሳድጉ የፊስካል ጥናቶችን ማካሄድ እና የበጀት አመዳደብን ከውጤት (program Budgeting) ጋር ማገናኘት።
- **አቅጣጫ** በበጀት ዝግጅት ወቅት ለካፒታል ፕሮጀክቶች ጥራትንና ጠቀሜታን መሰረት ያደረገ ጥብቅ የማጣሪያ (Screening) ስርዓት መዘርጋት።

3. **የመንግስትና የግል አጋርነትን (PPP) እና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋፋት**

- **ስትራቴጂ** ለትላልቅ የከተማ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች ከመንግስት በጀት በተጨማሪ የውስጥና የውጭ የግል ኢንቨስትመንትን መሳብ የሚያስችል የPPP ማዕቀፎችን በተግባር ላይ ማዋል::
- **አቅጣጫ** የከተማዋን የዕዳ ጫና የማይጨምሩ የፋይናንስ አማራጮችን (Asset Monetization እና የቦንድ ሽያጭ ጥናቶችን) መተግበር።

4. **የውስጥ ቁጥጥርና የኦዲት ስርዓትን ማጠንከር** (Accountability)

- **ስትራቴጂ** የአስፈፃሚ መ/ቤቶችን የውስጥ ኦዲት አቅም መገንባት እና የኦዲት ግኝቶችን በወቅቱ የማያስተካክሉ ተቋማት ላይ የበጀት እገዳን ጨምሮ ጥብቅ እርምጃዎችን መውሰድ።
- **አቅጣጫ** ከህዝብ እምባ ጠባቂ እና ከዋና ኦዲተር ጋር በመሆን የሀብት ብክነትን "የቅድመ-መከላከል" (Proactive Internal Audit) ስርዓት መዘርጋት።

5. **የተቋማዊ ብቃትና የሰው ሃይል ልማት** (Capacity Building)

- **ስትራቴጂ** በስራ ምደባና ደረጃዎች (ISCO-08 መደቦች) ላይ በመመስረት ለፋይናንስ ባለሙያዎች ቀጣይነት ያለው የብቃት ማረጋገጫ (Competency Framework) ስልጠና መስጠት።
- **አቅጣጫ** የቢሮውን የውስጥ አሰራር ግልጽ ከሚያደርገው የ"አገልግሎት ታክሶኖሚ ማንዋል" (Service Taxonomy Manual) ጋር የተጣጣሙ መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን ማጠናቀቅ።

ክፍል ሶስት

3.1. ተቋሙ ዋና ዋና ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዓላማዎችና ተግባራት እንዱሁም የሚጠበቁ ውጤቶች እና ማስፈጸሚያ በጀት

3.1.1. የቁልፍ ስራዎች እቅድ፦

የተቋሙ ቁልፍ ተግባራት ክብደት (62%)

ስትራቴጂክ ግብ 1:- የተቋም ግንባታና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ማሳደግ (25%)

1. አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል እርካታን ማሳደግ (ክብደት=4%)

1.1.1 በተቋም የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እንዱሰጡ ማድረግ

1.1.2 በአገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋለውን የሌብነትና የብልሹ አሰራር ማክሰሚያ ስርዓት በመዘርጋት መተግበር

1.1.3 አገልግሎት በስታንዳርድ የማይሰጡ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ

1.2 ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር አገልግሎትን ማሻሻል (ክብደት=2%)

1.2.1 በተቋሙ ምቹ የመስተንግዶ ስርዓት በመዘርጋት እንግልት እንዲቀንስ ማድረግ(አቅጣጫ ጠቋሚ፣ የመረጃ ዲስክ፣ የእንግዳ ማረፊያ፣ አስተያት መስጫ፣ የሠራተኛ ባጅና የጠረጴዛ ባጅ፣ ከተገልጋይ የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ እና ምቹ ምድረ ግቢ)

1.2.2 ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተገልጋችን የአገልግሎት ተደራሽነት የማረጋግጥ በአማራጭ መንገድ አገልግሎት መስጠት (ራምፕ ፣ ስልክ፣ ሊፍት)

1.3 ብዙሃን መገናኛ አውታሮችን በመጠቀም የአገልግሎት ውጤታማነት ማረጋገጥ (ክብደት =3%)

1.3.1 የሚዲያ ሽፋን በመስጠት የተገልጋይና የአገልጋይ መድረክ በመፍጠር በቋሚነት እንዲሳተፉ ማድረግ (ፓናል ውይይት፣ የቴሊቪዥን ገለፃ ፣ኢ.ፍ ኤም 96.3 .....ወዘተ)

1.3.2 ከተገልጋይ በተሰጡ ግብዓቶች መሰረት አገልግሎት እንዲሻሻል ማድረግ

1.4 ተቋማዊ አቅም ግንባታ ስርዓት በመዘርጋት የሰራተኛው የመፈጸም አቅም ማጎልበት (ክብደት =4%)

1.4.1 ተቋማዊ የክፍተት ዳሰሳ ስራ በመስራት የሰራተኞችን የማህበራዊና የቴክኒክ ብቃት ክፍተት መመላት

1.4.2 ተቋማዊ የዕውቀት አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ

1.4.3 ወርቃማ ሰኞ/አብሮነት/ መድረክ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ማድረግ

1.5 ተቋማዊ ውጤታማነት በማሻሻል የሰራተኛና የተገልጋይ እርካታ ማሳደግ (ክብደት =5%)

1.5.1 የቀነሰ የተቋሙ የሰራተኛ ቅሬታ፣

1.5.2 የሰራተኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት መስራት

1.5.3 የተቋሙ የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳ ጥናት መስራት

1.6 በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሰጡ አገልግልቶች ውጤታማነት ማሻሻል (ክብደት=4%)

1.6.1 በተቋም ደረጃ በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሠጡ አገልግሎቶች የመለየት ስራ መስራት

1.6.2 ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ ማድረግ

1.7 የአዳዲስ አሰራርና ፈጠራ ልምዶችን ማሳደግ (ክብደት =3%)

1.7.1 የተቋሙ አፈጻጸም ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲተገበሩ ማድረግ

1.7.2 የተፈጠሩ አዳዲስ ስራዎች እንዲቀመሩ በማድረግና በተቋም ደረጃ በመግባባት የስራ ክፍልች የማስፋት ስራ መስራት

1.7.3 አዳዲስ ስራዎች በመተግበራቸው የተገኙ ተጨባጭ ውጤቶችን ማስፋት

2 ስትራቴጂክ ግብ 2:- የከተማ መልካም አስተዳደር ችግር መፍታት፣ የአቤቱታ መወሰንና የማስፈጸም አቅም ማጎልበት እና ተቋማዊ የቅንጅት፣ የትብብርና የድጋፍ አሰራር ስርዓት ማሻሻል (ክብደት = 25%)

2.1 የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ቅሬታን የመቀነስ አሰራን ማሳደግ (ክብደት=7)

2.1.1 በህዝብ የሚነሱና በየደረጃው የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና የቅሬታ ምንጮችን መለየት

2.1.2 የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመቶኛ

2.1.3 በተገልጋይ የቀረበ ቅሬታና አቤቱታ አሰራሩን ጠብቆ የተሰጠ ምላሽ በመቶኛ

2.1.4 በተገልጋይ በአንድ ማዕከል ላይ የቀረበ ቅሬታና አቤቱታ የተሰጠ ምላሽ በመቶኛ

2.2 የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ማሳደግ፤ (ክብደት = 3)

2.2.1 የግንዛቤ እና ስርፀት የተፈጠረ መድረክ እና የተሳታፊ የሰው ኃይል ብዛት

2.2.2 የተወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነት አፈፃፀም በመቶኛ

2.2.3 በየደረጃው በአፈፃፀም ሂደት በታዩ ችግሮች ተጠያቂነት ማረጋገጥ በመቶኛ

2.3 የሕዝብና፣ሲቪል ማኅበራትና የግል ሴክተር ተሳትፎ ስርዓትን ማሳደግ፤ (ክብደት = 3)

2.3.1 ተቋም ተኮር ሲቪል ማህበራት የተለዩ ብዛት

2.3.2 በጋራ ፍላጎት መሠረት የተዘጋጀ መድረክና ተሳትፎ

2.4 ተቋማዊ ውጤታማነትን ማሳደግ፤ (ክብደት = 3)

2.4.1 በመልካም አስተዳደር ችግርና ቅሬታና አቤቱታ ምንጮች ዙርያ የተደረገ ጥናት ብዛት

2.4.2 የጥናት ውጤቱ ጥቅም ላይ ለማዋል የተፈጠረ የስልጠና እና ስርፀት መድረክ ብዛት

2.4.3 የተደረገው ጥናትና የተሰጠው ስልጠና ፋይዳ የሚያሳይ የግምገማ ሰነድ

2.5 ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት እና አተገባበርን ማሳደግ (ክብደት=6)

2.5.1 በስታንዳርዱ መሰረት በተቋሙ የተለዩና በጋራ ያቀዱ ተቋማት ብዛት

2.5.2 እቅዱን ለማሳካት በአፈፃፀም ሂደት የተደረጉ የጋራ ግምገማዎች

2.5.3 በቅንጅታዊ አሰራር ትግበራ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ የግምገማ ሰነድ

2.6 የቀዳማዊ ልጅነት ሥራዎች አፈፃፀምን ማሳደግ፣ (ክብደት = 3)

2.6.1 የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት አሰራር ሥርዓት ለመተግበር የተሰራ ስራ

2.6.2 ግብዓት የተሟላላቸውና አገልግሎት እየሰጡ ያለ የህፃናት ማቆያዎች ብዛት

2.6.3 የኢንሼቲቭና የሰው ተኮር ስራዎችን ውጤታማነት ግምገማ ሰነድ

3 ስትራቴጂክ ግብ 3:- የዕቅድ/ሪፖርት ዝግጅት፣ የኢንሸቲቭ ስራዎች አሰራር ሥርዓትን ማጎልበት (ክብደት=12%)

3.1 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ እንዲሁም ተናባቢነትን ማረጋገጥ(ክብደት=4%)

3.1.1 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድ/ክለሳ ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ

3.1.2 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጅትና መላክ

3.1.3 የተቋም እቅድ እና አፈጻጸም እስከ ሰራተኞች ያለው ተናባቢነት

3.2 በተቋማት የስራ አመራር ስርዓት ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=4%)

3.2.1 ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ለማረጋገጥ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተገኘ ውጤት፣

3.2.2 በየሩብ ዓመት አፈጻጸም ከዘርፍና ከቅ/ጽ/ቤቶች (ተጠሪ ተቋማት) ጋር በጋራ ስራ መገምገምና ዉጤታማ ማድረግ

3.3.3 በተለያዩ ዘዴዎች የተቋምን እቅድና አፈጻጸም ለባለ ድርሻ አካላትና ለተገልጋይ ማስተዋወቅና ማሳተፍ፣

3.3 የተቋም በጎ አድራጎት እና ኢንሸቲቪ ሥራዎችን ማጎልበት (ክብደት=4%)

3.3.1 የአቅመ ደካማ ቤተሰቦችን ቤት ማደስ

3.3.2 የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከልና መንከባከብ

3.3.3 ወላጆቻቸውን ያጡ ወይም የገቢ አቅማቸው ደካማ የሆኑ ወላጆች ሥር የሚተዳደሩ ህፃናትን መደገፍ

3.3.4 ማዕድ ማጋራት (ለማህበረሰብ እና ለሠራተኛ)

2019 በጀት ዓመት የአበይት ዋና ዋና ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዓላማዎች እና ዝርዝር ተግባራት፦

ግብ-1 የሀብት አመዳደብ እና አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣

ዓላማ-1. የልማት ሀብት አቅርቦት በ2018 ከነበረበት ብር 338 ቢሊየን፣ በ2019 502 ቢሊየን ብር ማድረስ፣

ተግባር-1. ለ2019 በጀት ድልድል የሚያገለግል የወጪ አስተዳደር ጥናት ሰነድ (ከ2018 እስከ 2021) ማከናወን

ተግባር-2. ለ2019 የኖርም፣ የቀመርና የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ክለሳ ጥናት በማከናወን ለበጀት ድልድል ማዋል፣

ተግባር-3. የ2019 የከተማውን ገቢ በዋና ዋና የገቢ ርእስ በመደልደልና በማፀደቅ ሰነዱን ለገቢ ሰብሳቢ ተቋማት ተደራሽ ማድረግ፤

ተግባር-4. አጠቃላይ በከተማው ለሚቀርቡ የአገልግሎት ማሻሻያ ክፍያ በማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ።

ተግባር-5. በንብረት ግብር አተገባበር ላይ ለባለሙያዎችና አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤

ተግባር-6. አንድ የንብረት ግብር ደንብ በማዘጋጀት እና በማጸደቅ ተግባራዊ ማስደረግ

ተግባር-7. በሁለት /ገቢዎች እና መሬት አስተዳደር ቢሮ/ የቤት ግብር አተገባበር ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ዓላማ-2. ለዘላቂ ልማት ዘርፎች በ2018 የተመደበ በጀት ከነበረበት 71.97% በ2019 ወደ 72% ማሳደግ፣

ተግባር-1. ለ2019 በጀት ዓመት ለዘላቂ ልማት የተደለደለውን በጀት መረጃ ማደራጀት፤

ተግባር-2. ለ2019 ለዘላቂ የልማት ዘርፎች የሚመደበውን በጀት የተቋማትን መረጃ ማደራጀት

ተግባር-3. የከተማ አስተዳደሩ የ2019 በጀት አጠቃቀም መረጃዎችን በማደራጀትና ሰነድ ማዘጋጀት

ተግባር-4. የከተማ አስተዳዳሩን የ2019 የትኩረት አቅጣጫዎችን መለየት መረጃዎችን ማደራጀት፤

ተግባር-5. ለ2019 የዘላቂ የልማት ግቦች በተለየው የትኩረት አቅጣጫ መሰረት በጀት ለተቋማት መመደብ፣

ዓላማ-3. የከተማውን የበጀት አጠቃቀም በ2018 ከነበረበት 95% በ2019 ወደ 96% ማሳደግ

ተግባር-1. ለ2018 በጀት ዓመት የፀደቀውን በጀት ለባለበጀት መ/ቤቶች ማሳወቅ፤

ተግባር-2. ለባለበጀት መ/ቤቶች በበጀት አጠቃቀም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት፤

ተግባር-3. ጥቅም ላይ ያልዋለውን በጀት ለ ለውሳኔ በማቅረብ እጥረት ለገጠማቸው ተቋማት ሽግሽግ ማድረግ፤

ተግባር-4. ባለባጀት መ/ቤቶች ለ2019 በሚሰጣቸው የበጀት ጣሪያ መሰረት ድልድል ሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

ተግባር-5. ለ2019፣ 82 ባለበጀት መ/ቤቶች እና 11 ክፍለ ከተሞች በድምሩ=93 ለባለበጀት መ/ቤቶች የቀረበውን የበጀት ጥያቄ መነሻ በማድረግ የበጀት ድልድል ማካሄድ፤

ተግባር-6. ለ2019 ከባለበጀት ከተቋማት የቀረበውን የበጀት ጥያቄ መነሻ በማድረግ የበጀት ስሚ ማካሄድ፤

ተግባር-7. ለ2019 የተደለደለውን ረቂቅ በጀት ለከተማ አስ/ም/ቤት በማቅረብ ማስተቸትና ማፀደቅ፤

ተግባር-8. ከተባበሩት መንግስታት ለተቋማት የተደለደለውን የእርዳታ በጀት ክትትልና ድጋፍ፣ ግብረ መልስ መስጠት፣

ተግባር-9. ከተባበሩት መንግስታት ለተቋማት የተደለደለውን የእርዳታ በጀት መድረክ በማዘጋጀት መገምገም፤

ተግባር-10. በበጀት አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ስርአት ላይ ከተቋማት ለተወጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤

ዓላማ-4. የፋይናንስ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የተደረገባቸው የመንግስት ፕሮጀክቶችን ብዛት በ2018 ከነበረበት 86% በ2019 ወደ 88% ማድረስ፤

ተግባር-1. የመንግስት ፕሮጀክት ላይ በየወሩ ክትትልና ግምገማ ማከናወን፤

ተግባር-2. ክትትልና ግምገማ ለተከናወነባቸው ተቋማት በየሩብ ዓመቱ ግብረ መልስ መስጠት፤

ተግባር -3. ክትትልና ድጋፍ ለሚከናወንባቸው ፕሮጀክቶች ፕሮፋይሎችን ማደራጀት

ተግባር -4. ተጠናቀው አገልግሎት የማይሰጡና የቆሙ ፕሮጀክቶችን በመለየት ችግራቸው እንዲፈታ አስፈጻሚ አካላት ምክረ ሃሳብ በሰነድ ማቅረብ፤

ተግባር -5. በበተለያየ ጊዜ በአስፈጻሚ አካል የዋጋ ማሻሻያ ውሳኔ የተላለፈባቸውን ፕሮጀክቶች ያሉበትን ደረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በሰነድ ማሳወቅ፤

ተግባር -6. ውለታቸው ከተቋረጡ ፕሮጀክቶች መመለስ የሚገባውን የመንግስት ሀብት የመረጃ ሰነድ በማሰባሰብና በጋራ እንዲገመገም ማድረግ አፈጻጸሙን መከታተል፤

ተግባር -7. ከተቋማት ለተውጣጡ የፕሮጀክት ክትትል ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

ተግባር -8. ከተቋማት ከተውጣጡ የበጀት ዝግጅት መሪዋች እና የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ባለሙያዎች ጋር መድረክ በማዘጋጀት የፕሮጀክቶች እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ፤

ተግባር-9. የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓትን ለማሻሻል የሚረዳ አንድ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሶፍት ዌር እንዲበለጽግ ጥያቄ ማቅረብና አፈጻጸሙን መከታተል፤

ዓላማ-5. የሲማድ ፕሮጀክቶችን ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ በ2018 ከነበረበት 352 በ2019 ወደ 357 ማድረስ፤

ተግባር-1. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክቶችን ዕቅድ ተቀብሎ በማበልጸግ የትግበራ ስምምነት መፈጸም፤

ተግባር-2. የሲ.ማ.ድ. በገቡት የፕሮጀክት ውል ስምምነት መሰረት እየፈጸሙ መሆኑን በመስክ ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት፣

ተግባር-3. የሲ.ማ.ድ.የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ሲያቀርቡ ከሚመለከታቸው ጋር የመስክ ማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ፣

ተግባር-4. የሲ.ማ.ድ ለበጎ አድራጎት አግልግሎት የተሰጠ ይዞታ ለታለመለት ዓለማ መዋሉን በመስክ ክትትል ማድርግ፤

ተግባር-5. ለየሲ.ማ.ድ ለበጎ አድራጎት አግልግልት የተሰጡ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በፋይናንስ ቢሮ ስም እንዲመዘገብ ማድረግ፤

ተግባር-6. ለየሲ.ማ.ድና የመንግስት አካላት የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ውይይት ማካሄድ፤

ዓላማ-6. ከሲ/ማ/ድርጅቶች በዘላቂ የገቢ ማስገኛ መስክ ተጠቃሚ ያደረጉ ድርጅቶች ፕሮጀክትን በ2018 42 ከነበረበት በ2019 46 ማድረስ፤

ተግባር 1. የአጭር ጊዜ የሙያ ስልጠና በመስጠት የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ እንዲሰማሩ የፕሮጀክት ስምምነት ከፈፀሙ ድርጅቶች ውስጥ በውላቸው መሠረት ለተጠቃሚዎች ድጋፍ ማድርጋቸውን በክትትልና ድጋፍ ማረጋገጥ፤

ተግባር.2. የፕሮጀክት ስምምነት ከፈፀሙ ድርጅቶች ውስጥ ለተጠቃሚዎች የገቢ ማስገኛ ድጋፍ የሚሰጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን መለየት እና በገቢ ማስገኛ ስራ ማካተታቸውን ማረጋገጥ

2019 በጀት ዓመት ፋይናንስ ዘርፍ እቅድ

ግብ-2. የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፣

ዓላማ-7. ወርሀዊ ሂሳባቸውን ወር በገባ እስከ 7 የዘጉ ተቋማት በ2018 ከነበረበት 90% በ2019 92 % ማድረስ

ተግባር 1. ለ83 ሂሳብ ሪፖርት አቅራቢ ተቋማት ጣሪያ መመስረትና ለ11 ክ/ከተሞች የመደበኛና ካፒታል በጀት ማስተላለፍ፣

ተግባር 2. የ83 ሴ/መስሪያ ቤቶች እና 11 ክ/ከተሞች ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርቶች በሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና መመሪያ መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ተግባር 3. ለሂሳብ ሪፖርት አቅራቢ ተቋማት ጥያቄ ሲያቀርቡ የባንክ ሂሳቦችን መክፈት፣ መዝጋት እና የፊርማ ለውጥ ለባንክ ማሳወቅ እና በዳታ ቤዝ መያዝ፣

ተግባር 4. የ2018 በጀት ዓመት የአስተዳደሩን ገቢና ወጪ ሂሳብ በመዝጋት በሰነድ ማደራጀት፤

ተግባር 5. የ2018 የተዘጋውን የከተማውን የሂሳብ ሪፖርት መረጃ በማደራጀት በዋና ኦዲተር መ/ቤት ማስመርመር፤

ተግባር 6. በበጀት ዓመቱ ልዩ ልዩ ገቢዎችን መቀበል እና ባንክ ገቢ መደረጉን መከታተል እና ማረጋገጥ፤

ተግባር 7. በተቋማትን የሂሳብ አሰራር ስርአት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት፤

ተግባር 8. በጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና በሂሳብ አያያዝ ስርአት ላይ ለፋይናንስ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤

ዓላማ-8. ውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በ2018 ከነበረበት 40% በ2019 ወደ 42 % ማስቀነስ፤

ተግባር-1. በ83 ሴክተር መ/ቤቶችና 11 ክፍለ ከተሞች የውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የእድሜ ትንተና በመስራት የተደራጀ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር-2. የሂሳብ ሪፖርት አቅራቢ ተቋማት በአመዘጋገብ ስህተት መረጃ ሲያቀርቡ የተጣራ ሃብት /5601/ በመንካት በስህተት የተመዘገበውን ተሰብሳቢ ሂሳብ ማስተካከያው ምዝገባ መከናወኑን ክትትል በማድረግና ማስቀነስ፤

ተግባር-3. እስከ 2018 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ 42% ማስቀነስ፤

ተግባር-4. በ83 ሴክተር መ/ቤቶችና 11 ክፍለ ከተሞች የውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ የእድሜ ትንተና በመስራት የተደራጀ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር-5. የሂሳብ ሪፖርት አቅራቢ ተቋማት በአመዘጋገብ ስህተት መረጃ ሲያቀርቡ የተጣራ ሃብት /5601/ በመንካት በስህተት የተመዘገበውን ተከፋት ሂሳብ ማስተካከያው ምዝገባ መከናወኑን ክትትል በማድረግና ማስቀነስ፤

ተግባር-6. እስከ 2018 ውዝፍ ተከፋይ ሂሳቦችን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ 42% ማስቀነስ፤

ዓላማ-9. የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የተገበሩ ወረዳዎች፣ጤና ጣቢያዎችና ትምህርት ቤቶች ሽፋን በ2018 100% ከነበረበር በ2019 ወደ 100% ማስቀጠል፤

ተግባር 1. የ2018 በጀት ዓመት በቻናል አንድ ፕሮግራም የሚገኙ 3 ፕሮጀክቶች ሂሳብን በመዝጋት በፌደራል ዋና ኦዲተር ማስመርመር፤

ተግባር 2. በቻናል አንድ ፕሮጀክቶች ላይ ለክ/ከተማና አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ መስጠት

ተግባር 3. ከወረዳ የልማት ቡድን አባላት ጋር የቅድመ በጀት ውይይት ማድረግ።

ተግባር 4. ለቻናል አንድ ፕሮግራሞች የተመደበውን በጀት በሩብ አመቱ እቅድ መሰረት መጠቀም።

ተግባር 5. የቻናል አንድ ፕሮጀክቶችን የሂሳብ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በማጠቃለል ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ፣

ተግባር 6. ለወረዳ እና ክ/ከተማ የማህበራዊ ተጠያቂነት ተጠሪዎች በማህበራዊ ተጠያቂነት አተገባበር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 7. ከማህበራዊ ተጠያቂነት ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ የምክክር መድረክ ማካሄድ፤

